# ከታሪክ ጋር የተጣሉ ጎሠኞች።

ከአባ ታቦር

በጎሣ ተደራጅተዉ እራሳቸዉን ከኢትዮጵያ ማህበረሰብ በማግለል፤መገንጠልን የመጨረሻ ግባቸዉ ያደረጉ ድርጅቶችን ወደ አንድነቱ መመለስ የሚቻል አይደለም።ቢቻል ኑሮ፤ሻዕብያና ወያኔ ኢትዮጵያዊያን በሆኑ ነበር።

የደርግ መንግሥት፤እነኝህን ኃይሎች ወደ አንድነቱ ለመሳብ፤ያሎጣዉ ዳገት፤ ያሎረደዉ ቁልቁለት አልነበረም።ሻዕብያና ወያኔ፤ከድክመቱ እየተማሩ እያሾፉበት፤ መንግሥት በመንግሥትነቱ የሚሠራዉን በቅጡ እንዳያከናዉን መሰናክል ሆነዉ ቆይተዉ፤በመጨረሻ የራሱ ድክመት ተጨምሮበት፤ሊጥሉት ችለዋል።

ኦነግና ኦብነግ የሻዕብያ ጉዳይ ፈጻሚዎች ናቸዉ።ሻዕብያ በጧት ያስጨበጣቸዉን፤ከኢትዮጵያ የመገንጠል አጀንዳ ተቀብለዉ፤ ትናንሽ የጎሣ መንግሥታትን ከማቋቋም በስተቀር፤በሌላ የአንድነት ጉዳይ አይሞከሩም ።

"ቁርጥ ያጠግባል" ይላሉ አባቶቻችን።የእነኝህ ድርጅቶች አቋም በቅጡ ስለሚታወቅ፤የአንድነት ኃይሉ፤በዚህ ላይ የሚያጠፋዉ ጊዜና ጉልበት ሊኖር አይገባም።የግንቦት 7 ንቅናቄ የሚደክመዉ በከንቱ ስለሆነ፤ "ላም አለኝ በሰማይ ጥጃዋንም አላይ" ብሎ፤አንድነት ኃይሎችን ወደ ማጠናከር ሥራዉ ቢመለስ ይበጀዋል።

ፀረ አንድነት እንዴት ተከሰተ ? ሻዕብያ ፀረ አንድነት ፀረ ኢትዮጵያ እንዴት ሊሆን በቃ ? ሀገሪቱስ በጎሣ እንድትከፋፈል ለምን ፈለገ ? ከዚህ ቀጥሎ ለጥያቄዎቹ መልስ ለመስጠት እሞክራለሁ።ታሪካዊ አመጣጡንም አሳያለሁ።

ጣልያን ከኢትዮጵያ ከተባረረ በኋላ፤በእንግሊዝ ዘመን፤በኤርትራ "ኢትዮጵያ ወይም ሞት" የሚል መፈክር ያነሱ ኤርትራዊያን መነሳታቸዉ ይታወቃል።

በሌላ በኩል ደግሞ፤ጥቂት ሰዎች የሚያራግቡት፤የአማራ ጥላቻም እንደነበር ይታወሳል። ከእነኝህ ፀረ አማራ ግለሰቦች መካከል ዋናዉ፤የትግራይ ተወላጁ፤ወልደ ዓብ ወልደ ማርያም የተባለዉ ሲሆን፤ከትንሽ ጊዜ በኋላ ደቀ መዛሙርቱ፤የሻዕብያና የወያኔ መሪዎች፤ጥላቻዉን ከመምህሩ በላይ አናፈሱት። የጥላቸዉ መነሻ "አምሐራዉ መንግሥታችን ከመቀማቱም በላይ ለድህነት ዳርጐ አቅመ ቢስ አድርጐን ቆይቷል" እሚል ሲሆን፤በተለይ በሸዋ አማራ ላይ ጥርሳቸዉን እንደነከሱ ቆዩ።ተቀማን የሚሉትንም ሥልጣን መልሶ ለመጨበጥ ጥረት ጀመሩ ።

ይህን መሰሪ የጎሣ ጥላቻ፤ከአማራዉ ዉጭ ያለዉ ሁሉ እንዲገነዘበዉና ወደ እነሱ እንዲጠጋ ብርቱ ጥረት አደረጉ። "የአምሐራ ኢምፓየር" እያለ ሻዕብያ በሚጠራት ኢትዮጵያ፤ሁሉም ጎሣ በአንድነት ስም ተጠፍሮ ተይዞ፤ የአገዛዝ ቀንበር እንደተጫነበት ተደጋግሞ ተነገረ።የአማራ ቋንቋም በብሔር ብሔረሰቡ ላይ በግዴታ እንደነጫነ ተሰበከ።

ሁሉንም በሀቅ ስንመለከተዉ፤አንድ እንደ ኢትዮጵያ ያለ፤የብዙ ሽህ አመት የመንግሥት ታሪክ ያለዉ ሀገር ቀርቶ፤አዲስ የተፈጠረ ሀገርም ቢሆን ሲመሰረት፤በዉስጡ ያሉ ጎሣዎች፤ቋንቋዎች፤ባህሎች ሁሉ በአንድ ላይ ተዋህደዉ፤ወይም ተጨፍልቀዉ፤አንድ ጠንካራና የታወቀ መንግሥት ማቆም የተለመደ ነዉ። በጥቂቱ ምሳሌ ለማቅረብ ያህል፤የከማል አታቱርክ ቱርክን፤የቢዝማርክ ጀርመንን፤የጋሪባልዲ ጣልያንን፤የክሮምዌል እንግሊዝን፤ የታላቁ ጴጥሮስ ሩስያን መመልከት ይበቃል።

የሻዕብያና የወያኔ መሪዎች፤ ይህ ጠፍቷቸዉ አይደለም። ግን በጥላቻና በምቀኝነት በአማራ ላይ ልባቸዉ የተቃጠለ በመሆኑ፤የጋራ አባቶቻችን ካቆዩዋት ጠንካራና ታሪካዊት ኢትዮጵያ ይልቅ፤በጎሣ የተበታተነች ደካማ ሀገር መፍጠር ወደ ዓላማቸዉ የሚያደርሰ መስሎ ስለታያቸዉ፤ ይህን መንገድ መርጠዋል።

ሻዕብያና ወያኔ አማራዉን ከመጥላታቸዉም በላይ፤ እንደ ሰይጣን የፈሩታል። በመሆኑም ከአማራዉ ላይ አለ የሚሉትን ሥልጣን ለመቀማት፤ ሀገሪቱን በጎሣ መከፋፈል እንደ መፍትሄ ይዘዉታል።የከፋፍለህ ግዛዉ ዘዴያቸዉንም በፍጥነት ተግባራዊ አደርገዉታል።

የሀገራቸዉን ታሪክ በቅጡ ያልመረመሩት፤የብሔር ብሔረሰብን ምንነት የማያዉቁት ወያኔና ሻዕቢያ ጠባብነትን በማምለክ፤ተባብሮና ተዋዶ የኖረዉን የሀገራችን ሕዝብ አቆራረጡት።በግጦሽ፤በድምበር፤በሃይማኖት፤እንዲራኮት አደረጉት።የብሔር ብሔረሰብ ጥቅም አስመስለዉ፤ለከፋፍለህ ግዛዉ ዘዴያቸዉ ሲራወጡ፤አማራ አማራነቱን እንኳ አያዉቅም ነበር።ጎንደሬ፤ወሎዬ፤ጐጃሜ፤ሸዌ እየተባባለ ከመኖር በስተቀር የጎሣ ስሜት አልነበረዉም።ለዚህ ነዉ ከትግሬዉ ፤ከጉራጌዉ፤ከኦሮሞዉ፤ከወላይታዉ፤ከሌላዉ ጋር ተጋብቶ ተዋልዶ ተደበላልቆ የኖረዉ።መንግሥቱም ቢሆን የአማራ መንግሥት ነበር ለማለት አይቻልም።ከሁሉ ብሔር ብሔረሰብ የተወጣጣ ኃይል ነበር ሀገር የሚያስተዳድረዉ።ቤተ መንግሥት የተጠጋ ብልጣብልጥ ሁሉ፤ሥልጣን ላይ በቀላሉ ይወጣ ነበር።በኋላ ደግሞ የተማረ ሁሉ፤ችሎታ የነበረዉ ሁሉ፤ ለሥልጣን የሚያግደዉ አንዳች ነገር አልነበረም።

በደርግ ዘመን፤ከልዩ ልዩ ጎሣ እየተመረጡ፤ርዕሰ ብሔር እስከመሆን ደረጃ የደረሱ፤ ጄ/ አማን ሚካኤል አንዶም - ትግሬ ኤርትራዊ፤ ጄ/ ተፈሪ በንቲ - ኦሮሞ፤ ኮ/ መንግሥቱ ኃይለ ማርያም - ኦሮሞ/አማራ ነበሩ።

ሻዕብና ወያኔ የተባበረ ሕዝብ ታላቅነት የሚያስፈራቸዉ ስለሆኑ እርምጃችን ወደ ኋላ ጐትተዉታል።ከደርግ ላይ ሥልጣን እንደነጠቁ፤የነበረዉን ከመሰረቱ ሳይነቃቅሉ፤የሚገባዉን ይዘዉ ቢቀጥሉ ኖሮ፤አሁን ግራ ቀኙ ከደረሱበት የፖለቲካ ትርምስ ዉስጥ አይገቡም ነበር።ይልቅስ በአፍሪቃ መሪ ሀገር፤ በዓለም ደግሞ ዛሬ በልጽገዉና መጥቀዉ ከሚታዩት፤ከብራዚልና ከሕንድ ጐን በተሰለፍን ነበር።

ሻዕብያና ወያኔ ሰላሳ አመት ሙሉ ተዋግተዉ፤በለስ ሲቀናቸዉ ሀላፊነታቸዉን ዘንግተዉ፤ለጦርነት የማገዱትን የኤርትራና የኢትዮጵያ ሕዝብ ሳይጠቅሙ ቀሩ።መፃኢ እድሉንም ዘጉበት።ሀገሪቱን ለሁለት ከፍለዉ፤ሁለት አቅመ ቢስ መንግሥታት አቁመዉ፤እርስ በእርሳቸዉ እየተራኮቱ፤ወርቃዊ እድላቸዉን አበላሹ።ጠቅላላ የኢትዮጵያን ሕዝብ ወርቃዊ እድልም መና አስቀሩት።

ከፋትና ተንኮልን እንደ ጀብዱ የሚቆጥሩት፤መለስ ዜናዊና ኢሳይያስ አፈወርቂ፤እነሱ እራሳቸዉ ትንንሽ ሆነዉ፤ሀገራችን ትንሽ አደረጓት። አቅመቢስ ሆነዉ፤ሀገራችን አቅመ ቢስ አደረጓት።ወደ 21ኛዉ ምዕተ አመት ያመራችዉን ሀገራችን ወደ 18ኛዉ ምዕተ አመት አወረዷት።ግራ ቀኝ ሕዝቡ

ነቅቶ አምዘግዝጐ እንዳይጣላቸዉ፤በየጎሳቸዉ ጦር ዉስጥ እራሳቸዉን ደበቁ። በእነኝህ ተንኮለኛ መሪዎች ምክንያት፤በሰላሳ አመቱ አዉዳሚ ጦርነት፤በግራ ቀኙ ከሚሊዮን ያላነሰ ወገናችን እንደ ቅጠል እረግፏል።ታዲያ የተገኘዉ ትርፍ፤ድህነት፤ዉድቀት፤መከራና ዉርደት፤ጥላቻና ተስፋ ቢስነት ሆነ።እነኝህ ጠባብና አሳብ ስንኩል አምባ ገነን መሪዎች ወደ አእምሯቸዉ እስካልተመለሱ ድረስ መከራችን ይቀጥላል።

ሻዕብያ በራሱ አምሳል የቀረፃቸዉ ኦነግና ኦብነግ፤የተሰጣቸዉን ተልዕኮ ሳይፈጽሙ አይተኙም።ከአንድነት ኃይሎች ጋር መወገን ማለት“በኢምፓየሩ” እንደገና መዋጥ ማለት ስለሆነ፤የተሰጣቸዉን መመሪያ ተግባራዊ ከማድረግ በስተቀር፤ለሌላ ተልዕኮ አይሰለፉም።እንደ ሻዕብያ እነሱም የኢትዮጵያ ኮሎኒ መሆናቸዉን፤ለዓለም ነፃ ሕዝቦች አስታዉቀዋል።ኦነግ በቅርቡ ለተባበሩት መንግሥታት ሸንጐ ይህንኑ የሚመለከት አቤቱታ አሰምቷል።ዛሬም በዌብ ሳይቱ (web site) ላይ “ኦሮምያ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ናት” በማለት ጽፎ በማሳየት ላይ ይገኛል።

ሻዕብያ፤ ኤርትራ የኢትዮጵያ “ቅኝ ግዛት” ነች፤ ዓይኔን ግምባር ያድርገዉ በሎ ተከራክሮ፤ በመጨረሻም ተዋግቶ፤ነፃነትን ካስገኘ፤ኦነግም በዚያዉ መስመር ኦርምያን ነፃ የማያወጣበት መክንያት የለም ብሎ ገምቷል።

አብዛኞቹ በዚህ በወያኔ ዘመን ጐልተዉ የወጡት የኦሮሞ ድረጅቶች፤ የኢትዮጵያ አንድነት እንደተጠበቀ ሆኖ፤በዋናነት የኦሮሞን ሕዝብ መብት ለማስጠበቅ የተነሱ ናቸዉ።በክቡር አቶ ቡልቻ ደመቅሳ የሚመራዉ፤የኦሮሞ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ኦፍዴን) የፕሮፌሰር መረራ ጉዲና፤የኦሮሞ ብሔራዊ ኮንገሬስ (ኦብኮ) በዚህ መንፈስ ብቅ ያሉ ድርጅቶች ናቸዉ።

እነኝህ ሁለት ድርጅቶች ከአምሳ አመት በፊት፤የኦሮሞ አባቶች ሜጫና ቱለማ፤ያነሱትን መፈክር ያነገቡ ስለሆነ፤ሰፊዉ ሕዝብ ዳር እስከዳር ተቀብሏቸዋል።ኦነግም እንደነዚህ ድርጅቶች ያባቶቹን ፈለግ ቢከተል ያምርበታል።

ኦነግ ከኢትዮጵያና ከኢትዮጵያዊነት ቀረቤታ የሚያርቁትን መንገዶች አስቀድሞ እንደቀየሰ፤የሚያሳዩ ምልክቶች አሉ።በለንደኑ ስብሰባ፤ቀጥሎም በአዲስ አበባዉ፤ሻዕብያና ወያኔ ኢትዮጵያን ሲያፈርሱ፤ከሀገሪቱ ሕዝብ መካከል ከመቶ 35ቱን ያህል እወክላሁ የሚለዉ ኦነግ፤ከአናሳዎቹ ጋር

ተሰልፎ ሀገር ሲያፈርስ መታየቱ ተስፋ የሚያስቆርጥ ነበር።ቀደም ብሎም በጦርነቱ ጊዜ፣በወለጋ ክ/ሀገር፣ከሻዕቢያ ጋር በመተባበር፣ያልታጠቀዉን የአማራ ሕዝብ፣በተለይ ሴቶችንና ሕፃናትን ቤት እየዘጋ ሲያቃጥላቸዉ መላዉ ዓለም በቴሌቭዥን ተመልክቷል።በኋላም በወተር፣በደንገጐ፣በጭላሎ፣ ነፍጠኛዉን እስከ ነፍሱ ገደል ሰዷል።የተረፈዉን በጥይት ቆልቶታል።ይህም ኦነግ ከኢትዮጵያዊነት እየራቀ መሄዱን፣ታሪኩን እረስቶ በሻዕቢያና ወያኔ በቀላሉ መታለሉን የሚያመለክት ነበር።

ኦሮምኛ አንዱ የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ቋንቋ እንደ መሆኑ መጠን፣ሁሉም እንዲነጋገርበት ማበረታታት ሲገባ፣ኦነግ ይባስ ብሎ፣ በላቲን ፊደል እንዲጻፍ ጥረት አደረገ። ሻዕቢያና ወያኔ የኢትዮጵያ ሕዝብ እሚነጣጠልበትን መንገድ የሚሹ ስለሆኑ፣ በዘመናቸዉ እንደዚህ ያለዉ ጉዳይ ከባለቤቱ ከኦሮሞ ድርጅት ሲነሳ፣ ዉስጥ ለዉስጥ እየሳቁ፣ ኦሮምኛዉ በላቲን ፊደል እንዲጻፍ ድጋፋቸዉን ሰጡ።የግዕዙ ፊደል በዘመን ብዛት ከኦሮምኛዉ ጋር ተዋህዶ፣ ከላቲኑ በበለጠ ጠቃሚ መሆኑ እየታወቀ፣የእራስን በማቃለል በሌላ ፊደል መተካት፣ምን ማለት ነዉ? ኢትዮጵያዊነትን ብሎም አፍረቃዊነትን የመጥላት ምልክት ነዉ።ጥንታዊ የኩሽ ልጅ ኦሮሞ፣ የኢትዮጵያ መሰረት መሆኑ እየታወቀ፣እንደ መጤ(alien) ተቆጥሮ፣ ፊደል ከአዉሮፓ በመዋስ ባይተዋር ያደረገዉ ኦነግ፣ ሀገራዊ በደል ፈጽሟል።ጥፋቱ ከይቅርታ በለይ ስለሆነ፣ንስሀ መግባት ይገባዋል።

በዚህ መጣጥፍ፣ኦነግ በሻዕቢያ እንክብካቤ ያደገ ድርጅትና ዛሬም ከሻዕቢያ ጉያ ያልወጣ መሆኑን ለማሳየት መክሬአለሁ።በዚህ ምክንያት፣ሻዕቢያ በጢት ያስጨበጠዉን ጥሎ፣ከአንድነት ኃይሎች ጋር ይወግናል ማለት ዘበት ነዉ።

የግንቦት 7 ንቅናቄ፣ በየመድረኩ የሚያቀርባቸዉ የኦነግ አባላት፣ዋናዉን የአንድነት ጉዳይ ገሸሽ ያደርጉና፣ "በትብብር ወያኔን አሶግደን፣ከዚያ በኋላ የኦሮሞ ጉዳይ፣ በዴሞክራሲያዊ መንገድ ይወሰናል" ይሉናል።ሻዕቢያ ከደርግ ዉድቀት በኋላ፣ በወያኔና በተባባሪዎቹ፣ ይህን የመሰለ እድል እንዳገኘ ይታወሳል። "ባርነት ወይም ነፃነት" የሚል የተዉተፈተፈ ምርጫ ቀርቦለት፣ የኤርትራ ሕዝብ በሪፈረንደም ነፃነቱን ተቀዳጀ እንደተባለ ልብ አድርገናል። የኢትዮጵያ መንግሥት "ወያኔ" የኤርትራን ለማወቅ የመጀመሪያዉ ሆነ።ከዚያ በኋላ፣ ዓለም ሁሉ ሉዓላዊ መንግሥትነቷን አወቀ።

ይህ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ፤በሻብያና በወያኔ የተፈጸመ ደባ፤ለሁለተኛ ጊዜ ይደገማል ብሎ ኦነግ ያምናል።

ግንቦት 7 ንቅናቄ፤ ይህን መሰሪ አካሄድ ባያጣዉም፤በሆደ ሰፊነት፤ "እስኪ እንተባበርና ባንድ ላይ ወያኔን እናሶግድ።ከዚያ በኋላ የኢትዮጵያ ሕዝብ እድል በተረጋጋ ሁኔታ፤በሁላችን ፈቃድ በዴሞክራሲያዊ መንገድ፤ መፍትሄ ይገኝለታል" ብሎ ይመኛል።ጉዳይዉን በይበልጥ በማብራራት ይቀጥልና "ከዚህም በላይ የኦሮሞ ሕዝብ ዉክልና በአንድ ድርጅት የተጠቃለለ ስለማይሆን፤ኦነግ ብቻዉን የሚወስነዉ ጉዳይ አይደለም።ስለዚህ ዙሮ ዙሮ ከሰፊዉ ሕዝብ ፈቃድ የሚያመልጥ ነገር የለም" ይላል።

የግንቦት 7 ንቅናቄ ቅን አስተሳሰብ የሚያዋጣ ቢመስልም፤ኦነግ የታጠቀ፤ የተደራጀ፤ ተቋም መሆኑ መዘንጋት የለበትም።ከዚህ በላይ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ዋና ደመኛ፤ ከሻዕብያ ጋር ያለዉ የጠበቀ ቁርኝት፤ግንቦት 7 ወደሚመኘዉ የለሰለሰና ኢትዮጵያዊ አቋም ይመጣል ተብሎ አይታመንም።

ኦነግ እንደ ሻዕብያ፤በኢትዮጵያ ታሪክ አያምንም።ታሪካችን በዉጭና በሀገር ዉስጥ ምሁራን ቁልጭ ብሎ ተጽፎ እያለ፤ የታሪክ አሻራችንም በሕያዉ ምስክርነት ቁሞ እየታየ፤ እነኝህ ፀረ አንድነት ድርጅቶች፤ ተረት ተረት ከማለት አልተቆጠቡም።

ታሪካዊት ኢትዮጵያ፤ በብረትና በእሳት የተገነባች ሀገር ናት።በጥንት ዘመን ሀገር ለማቆም፤ ሌላ መንገድ አልነበረም።ታዲያ ነገሥታቱ ሀገር ሲያቀኑ፤ በጉን ጥፋት ማስከተላቸዉ አልቀረም።አፄ ሚኒልክ ከመቶ አመት በፊት በደቡብና በምስራቅ ግዛት ሲያስፋፉ፤የተቋቋማቸዉን የኦረሞ ሕዝብ፤ ወግተዉ በኃይል አስገብረዉታል። የጥንታዊ አባቶቻቸዉ ግዛት የነበረዉን፤ ከግብፅ ወራሪ ኃይል ተጽዕኖ ነፃ አድርገዉ፤ ከእናት ሀገሩ ጋር ቀላቅለዉታል።ይህን ዘመቻ አስመልክቶ፤ኦነግ በምኒልክ ላይ የመረረ ወቀሳ ያሰማል።ግን ነገሩን ካንድ አቅጣጫ ብቻ ከማየት፤ጠለቅ ብሎ ታሪክን መመርመር ይገባዋል።

ከአፄ ምኒልክ የደቡብ ዘመቻ 300 አመት በፊት፤የኦሮሞ ሕዝብ ወደ ሰሜን የሀገሪቱ ክፍል መስፋፋቱን ልብ ማድረግ ይገባል። ከባሌ አካባቢ የተነሳዉ ኦሮሞ፤ በየአቅጣጫዉ ተጉዞ፤ ደጋዉን አገር በትንሽ ጊዜ ዉስጥ ሊያጥለቀልቀዉ ችሏል።በዚህ ወረራ በነባሩ ሕዝብ ላይ ጥፋት አልደረሰም አይባልም።በገዳ ሥርዓት፤ በሉባ ሠራዊት የተመራዉ ጦር፤ከፊቱ

የሚቋቋመዉን እያጠፋ፣ እየደመሰሰ፣ ሸዋን፣ ወሎን፣ በየምድርን፣ጎጃምን እንደወረረ ታሪክ ይመሰክራል። ኦነግና ኦነግን የመሳሰሉ የኦሮሞ ድርጅቶች፣ ይህን በታሪካችን ዉስጥ ጎልቶና ገዝፎ የሚታይ ክስተት፣ በቅጡ አይገነዘቡትም።ምኒልክም ሆነ ተስፋፊዉ የኦሮሞ ሉባ ሠራዊት፣በየዘመናቸዉ አገር ሲወሩ፣ ሕዝቡን በማርና በወተት እያባበሉ አልነበረም።በብረትና በእሳት እንጂ።

በመጨረሻ ኦነግ ከታረክ ተምሮ፣እንደ ሌሎች ድርጅቶች ኢትዮጵያዊ መሆን ይጠቅመዋል። በዴሞክራሲያዊ ሥርዕት፣የብዙሀን ወገን ሥልጣን የሚጨብጥ ስለሚሆን፣ እድሉ በእጁ ነዉ።ይህን ችላ ብሎ፣አናሳዎቹ የሄዱበትን የተንኮል መንገድ ቢከተል፣ኦሮምያንም ኢትዮጵያንም ያጣል።

ኢትዮጵያ በልጆቿ ብርቱ ተጋድሎ ለዘልዓለም ትኖራለች !!

abatabor@gmail.com